በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

**የሰበርመ.ቁ.-213330**

**ቀን:- ታህሳስ 13/2014 ዓ/ም**

**ዳኞች:-** ሸምሱ ሲርጋጋ

አስማየሁ ሹናሩ

ደረጀ አያና

**አመልካች/ቾች/ :-** እነ ወ/ሮ ማርታ በቀለ /2 ሰዎች/ ጠበቆች በሻዳ ገመቹ - አብርሃ አሸ / ቀረቡ

**ተጠሪ/ዎች/:-** እነ አቶ ሚልኪያስ መንገሻ /2 ሰዎች/

መዝገቡ ተከፍቶ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች /ቾች/ ነሐሴ 21 ቀን /2013 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በ ፌደራል ጠቅላይ /ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.199317 በ ግንቦት 25 ቀን 2013 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በመግለፅ በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው በሚል የቀረበ ነው:: በመሆኑም መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ትዕዛዝ ተሰጥቷል::

## ት እ ዛ ዝ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን የወራሽነት ማስረጃ ውጪዊ ዜጋ ስለሆኑ በአ/ቁ 922/2008 አንቀፅ 6/1/ መሰረት ስልጣን ባለው የኢትዮጲያ ቆንስላ ፅ/ቤት ተረጋግጦ ያልቀረበ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ተጠሪዎች ወራሽ አለመሆናቸውን አመልካቾች አልካዱም በማለት ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም አላቸው ሲል የወሰነበት አግባብነት ከአ/ቁ 922/2008 አንቀፅ 6/1/ እና ከፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር መ/ቁ 32282 አንፃር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩለ ሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ ብለናል::
2. የትዕዛዝ ግልባጭ ከመጥሪያ ጋር ለተጠሪዎች ደርሷቸው መልስ እና የመልስ መልስ በሬጅስትራር ፅ/ቤት በኩል ይቀባበሉ

መልስ ለመቀበል ለ 05/05/2014 ተቀጠረ፡፡ 9፡00

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ